ዓለም አቀፍ  የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization
P.O.Box  703913 , Dallas ,TX 75370-3913
USA    Tel 469 432 2435



**ሻለቃ ጥላሁን ቦጋለ**

**የጠላት መቅሰፍት አየር ኃይላችን !!!**

*ለዓላማቸዉ ከቆሙት ቆራጥ ጀግኖች*

*ሻለቃ ጥላሁን ቦጋለ በ1945 በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በወበራ አዉራጃ በደደር ከተማ ተወለዱ። የወታደር ልጅ በመሆናቸዉ አባታቸዉ ከነበሩበት አካባቢ ወደ ሐረር ከተማ ለግዳጅ በመዛወራቸዉ ሻለቃ ጥላሁን ቦጋለ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን የጨረሱት በዚህ ከተማ,ነዉ።*

*<<በሐረር ከተማ ወታደሮች ስለሚይ አባቴና ወንድሞቼ በዉትድርና ዉስጥ ስለሚኖሩ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ የሚነግሩኝን አንዳንድ ወታደራዊ ታሪኮች በሠራዊቱ ዩኒፎርምና በሥነ ሥርዓት አክባሪነቱ እንድሳብ ስላደረገኝ ገና በልጅነቴ የዉትድርና ፍቅር አደረብኝ። የስድስተኛ  ክፍል ተማሪ እያለሁ አስተማሪዬ የወደፊት ዓላማዬን በጠየቀኝ ግዜ የሰጠኋቸዉ መልስ የሠራዊቱ አባል ለመሆን ያለኝን ፍላጎትና ያሳደረብኝ ዝንባሌ የሚያንጸባርቅ ነበር >> ይላሉ ሻለቃ ጥላሁን ቦጋለ ።*

*ይህንን ከልጅነት ጀምሮ አብሮ ያደገዉን የዉትድርና ፍላጎታቸዉን ለመወጣት በ1962 በአየር ኃይል የበረራ ትምህርት ገቡ። በ1966 ትምህርታቸዉን ፈጽመዉ በም/መቶ አለቅነት ማዕረግ ተመረቁ ። ከዚህ ግዜ ጀምሮ በሰሜን ፣ በምስራቅ ፣ በደቡብና በሌሎች ጦር ግንባሮች በእናት ሀገራችን ላይ ጥቃት የሰነዘሩብንን ጠላቶቻችንን ለመደምሰስና*

ዓለም አቀፍ  የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር
**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**
**P.O.Box  703913 , Dallas ,TX 75370-3913**
**USA    Tel 469 432 2435**



*የሠራዊታችንን ጠንካራ ክንድ ለማሳየት በቁርጠኝነት ተሰለፉ ። ታዲያ ሻለቃ ከተሰለፉበት ግዳጅ ወደኋላ ባለማለትና በጀግንነት በመዋጋታቸዉ አያሌ ጀብዱዎች ለፈጽሙ ችለዋል ። ከጀብዱዎቻቸዉ መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸዉ ።*

*ወገን ከፍተኛ ቁጥር ባለዉ የወንበዴ ጦር ናቅፉ ላይ ይከበባል ። በቁጥር አነስተኛ የነበረዉ ጀግናዉ ሠራዊታችን ከጠላት ጋር ግብግብ ገጥሟል ። ሻለቃ ጥላሁንና የትግል ጓዶቻቸዉን ይህንን እንደተንዳን ይተራመስና ወገንን ከቦ የነበረዉን የገንጣይ ጦር በቦምብ ማጋየት ይጀምራሉ። በዚህ የጠላት ኃይል እንዲዳከም ያደርጋሉ ። ወዲያዉ ተከቦ ለነበረዉ የወግን ጦር እርዳታ የሚሰጡ አየር ወለዶች በጃንጥላ ሲወርዱ አደጋ እንዳይደርስባቸዉ ከጠላት ጥቃት ለማዳን ቁርጥ ሃሳብ ያደርጋሉ። እናም በወንበዴ ፀረ አዉሮፐላን ተኩስ ሳይደናገጡ የጠላትን ኃይል በተደጋጋሚ በቦምብ በመደብደብ አንገቱን በማስደፋት በወገን ላይ ሊደርስ የነበረዉን አደጋ አኮላሽተዋል ።*

*ሌላዉ የጀግንነት ዉሎአቸዉ ኢላበረድ ላይ የተፈጸመ ነዉ ። ወቅቱ ነፃ አዉጪ ሰራዊታችን የኢላበረዲን ህዝብና ከተማ ከከሃዲ ገንጣዮች እጅ ለማዉጣት የሚተናነቅበት ነበር ። የፍልሚያዉን ሁኔታ ስንመለከት የወገን ጦር ያለበት አካባቢ መልክአ ምድሩ ለዉጊያ አየሩ ለበረራ አመቺ አልነበረም ። በተለይ ከፍተኛ ዉግያ በተደረገበት በዚያ ዕለት ከተማይቱ በከባድ መሣሪያ ጭስ ታፍና ለእይታ በጣም አስቸጋሪ ነበር ። የወገንና የጠላት ጦር ትንቅንቅ ገጥሟል ።ሆኖም ሻለቃ ጥላሁንና ጓዶቻቸዉ ወንበዴን አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት የወገን ጦር ድልን እንዲቀዳጅ ከፍተኛና ሚና ከማድረጋቸዉም በላይ  ዋና አስተዋጽኦ በማድረግ ወገንን የሚያኮራና የማይረሳ  ተጋድሎ  አድርገዋል ።*

*ሻለቃ ጥላሁን በምስራቅ ግንባርም ለግዳጅ በተሰማሩ ጊዜ አገርንና ወገንን የሚያኮራ ጀብዱ የፈጸሙ ናቸዉ ። በ10/10/72 ዋርዴር በተደረገዉ ዉግያ በዝቅተኛ ከፍታ እየበረሩ ቅኝት በማድረግ ከአካባቢዉ ጋር በከፍተኛ ደረጃ ተመሳስሎ ሲያጠቃ የነበረዉን የጠላት ጦር ያያሉ ። ዒላማቸዉን አስተካክለዉም በርካታ ጠላትንና ንብረቱን ይቅመስልህ በማለት የጠላት ወታደሮችን ደመሰሱ ። ሽራ የለበሱ ተሽከርካሪዎችን ፣ ቢቲአሮችንና ልዩ ልዩ የስልት ተሽከርካሪዎችን አቃጠሉ ።ይሁን እንጂ በዚሁ ጦርነት ላይ አንዱ አበራሪ ጓዳቸዉ ግዳጁን ሲፈጽም ይመታባቸዉና ይወድቅባቸዋል ። በወቅቱ በአካባቢዉ መቆየት ከሚገባቸዉ በላይ ራሳቸዉን ለከፋ አደጋ አጋልጠዉ በመቆየትና ይህንኑ ጓዳቸዉን ለ30 ደቂቃ ያህል በመፈለግ የወደቀዉን አብራሪ ህይወት አትርፈዋል ። በምርኮ አማካኝነት ሊደርስ የሚችለዉን ስቃይ እንዲሁም ሊወጣ ይችል የነበረዉንም የወገን ጦር ሚስጢር እንዳይወጣ አድርገዋል ።*

*ጀግናዉ ሻለቃ ጥላሁን በፈጸሙት እጅግ በጣም ለሚያኮራ ጀብዱ በመንግስት የላቀ የጦር ሜዳ ጀብዱ ሜዳይ ተሸልመዋል ።*

*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!*

Email (feafww@gmail.com)    website (www.formerethiopianarmedforceworldwide.org)